*INTERME*

በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን
አዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ማ/ቅ/ጽ/ቤት
EHTIOPIAN REVENUE AND CUSTOMS AUTHORITY
A.A. KAIITY CUSTOMS BRANCH OFFICE

የውስጥመጻጻፊ

ቁጥር: ም/ሥ/የአድ/0040/09
ቀን: 24/10/2009

ለ፡- ጉምሩክ ስነ ስርዓት አፈፃፀም የስራ ሂደት
ለ፡- ደንበኞች አገልግሎት የስራ ሂደት
ለ፡- መጋዘን አስተዳደርና ቁጥጥር የሥራ ሂደት
ለ፡- ለህግ ማስከበር የስራ ሂደት
ለ፡- ድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት የስራ ሂደት
ለ፡- ጉምሩክ ጉዳች አቤቱታ አጣሪ ጽ/ቤት
ለ፡- ገቢ፣ተሰብሰቢና ዋስትና ሂስ\ቦች አስተዳደር ቡድን
ለ፡- ለትራንዚት ቡድን

ከ፡- ጉምሩክ ጉዳዮች ም/ስራ አስኪያጅ
አዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

የጉምሩክ ኘ/ል/ድ/ሥ/ዘርፍ በቁጥር 3.0/732/09 በቀን ሰኔ 21/2009 ዓ.ም በፃፈው ደብዳቤ የኮንቴነር እንደማንኛም ዕቃ ወደ ሀገር ውስጥ ሲገባ በታሪፍ አመዳደብ ደንብ መሠረት የታሪፍ መደብ ተለይቶ የታሪፍ ምጣኔ ተጥሎበት ቀረጥና ታክስ ሊሰበሰብበት የሚችል ዕቃ መሆኑ በቀረጥና ታክሱ ልክ ዋስትና እንዲያገዘበት የሚደረግ መሆኑን ገልፆ የጉምሩክ አዋጅ 859/06 ቀረጥና ታክሱን በመሸፈን ስለሚሰጥ ዋስትና የሚደነግግ ሲሆን በዋናነት ኮንቴነር ላይ የሚጠየቀው ዋስትና ኮንቴነሩ ከሀገር መውጣቱን ለማረጋገጥ መሆኑን አሳውቆናል፡፡

ስለሆነም በተላለፈው አሰራር መሰረት እንዲፈፀም እና የአሰራር ስርዓቱን ደንበኞች እንዲያውቁት እንዲደርግ እና በአፈፃፀም ወቅት የሚያጋጥሙ ችግሮች በሪፖርት እንዲቀርቡ እያሳሰብኩ የተላከውን 10 ገጽ ደብዳቤ በአባሪነት አያይዘን ልከንላችኋል፡፡

ከሰላምታ ጋር

ግልባጭ፣
- ለሥራ አስኪያጅ ጽ/ቤት
  አዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
ETHIOPIAN REVENUES AND CUSTOMS AUTHORITY

ቁጥር / Ref. No 3-0/732/09
ቀን / Date 21 ሰኔ 2009

የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ለሚፈፀምባቸው ቅ/ጽ/ቤቶች በሙሉ

በያሉበት፣

ጉዳዩ፡- <u>በጊዜያዊነት ወደ ሀገር ውስጥ ለሚገባ ኮንቴነሮች ዋስትና ስለሚያዝበት እና ከሀገር መውጣታቸው ተረጋግጦ ተመላሽ ስለሚደረግበት ሁኔታ የተሻለፈ የአሰራር ሥርዓት፣</u>

ኮንቴነር እንደማንኛውም ዕቃ ወደ ሀገር ውስጥ ሲገባ በታሪፍ አመዳደብ ደንብ መሠረት የታሪፍ መደብ ተለይቶ የታሪፍ ምጣኔ ተጥሎበት ቀረጥና ታክስ ሊሰበሰብበት የሚችል ዕቃ መሆኑ በቀረጥና ታክሱ ልክ ዋስትና እንዲያዝበት የሚደረግ መሆኑ ይታወቃል። በመሆኑም የጉምሩክ አዋጅ 859/06 ቀረጥና ታክሱን ለመሸፈን ስለሚሰጥ ዋስትና የሚደነግግ ሲሆን በዋናነት በኮንቴነር ላይ የሚጠየቀው ዋስትና ኮንቴነሩ ከሀገር መውጣቱን ለማረጋገጥ ነው።

ይሁን እንጂ ኮንቴነር ከሀገር መውጣቱን ለማረግገጥ የሚጠየቀው ዋስትና እና ያለው አሠራር በወጪ ንግድ ላይ የተሰማሩ ላኪዎች የኮንቴነር እጥረት እንዲያጋጥማቸው እያደረገ መሆኑን ከሚቀርቡ ጉዳዮች ለመረዳት በመቻሉ አሠራሩን የሚያሳልጥ እና የተለያዩ አማራጮችን ከግምት ውስጥ ያስገባ አሠራር መዘርጋት አስፈልጓል።

በዚሁ መሠረት ይህ ደብዳቤ ወጪ ከሆነበት ቀን ጀምሮ ከዚህ መሸኛ ደብዳቤ ጋር ተያይዞ በቀረበው የአሠራር ሥርዓት መሠረት አስፈላጊው የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ተፈፅሞበት እንድታስተናግዱ እየገለፅን፣ በአሰራሩ ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮች ካሉ በአስቸኳይ ለጉምሩክ ኘ/ል/ድ/ሥ/ዘርፍ እንድትሳውቁ አሳስባለሁ።

ከሠላምታ ጋር

ደበሌ ቃበታ

[illegible] ጉምሩክ ኘ/ል/ድ/ሥ/ዘርፍ

ግልባጭ

- ለክቡር ዋና ዳይሬክተር
- ለሕግ ማስከበር ሥራዎች ዘርፍ
- ለጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች ክትትልና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
- ለጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ኘሮግራምና ልማት ዳይሬክቶሬት
- ለደንበኞች አገልግሎት ዳይሬክቶሬት
- ለገቢ ሂሳቦች አስተዳደር ዳይሬክቶሬት

<u>ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን</u>

ለዘመናዊና ፍትሐዊ የታክስና ቀረጥ አስተዳደር ሥርዓት ግንባታ ተግተን እንሰራለን !!

ስ.ቁ / Tel.. 011 662 98 00
ፋ / Fax: 011 662 99 06
ኢሜል / Email: erca@ethionet.et
ድረ ገጽ / Website: www.erca.gov.et
ፖ.ሣ.ቁ / P.O.Box: 2559
አዲስ አበባ -ኢትዮጵያ
Addis Ababa, Ethiopia

- ለኤርፖርት ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለቃሊቲ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለአዳማ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለሞጆ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለድሬዳዋ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለባህርዳር ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለሐዋሳ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለመቀለ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለጅማ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለኮምቦልቻ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለጅግጅጋ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለሚሌ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለሞያሌ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለጋላፊ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለጅቡቲ ማስተባበሪያ ቅ/ጽ/ቤት

<u>በያሉበት፤</u>

# በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን

# በጊዜያዊነት ወደ ሀገር ውስጥ ገብቶ ተመልሶ የሚወጣ የባዶ ኮንቴነር ዋስትና አፈፃፀም ስርዓት ማንዋል

ሚያዚያ 2009

አዲስ አበባ

## 1. መግቢያ

ኮንቴነር እንደ ማንኛውም ዕቃ ታይቶ ወደ ሀገር ውስጥ ሲገባ በታሪፍ አመዳደብ ደንብ መሠረት ምጣኔ ተጥሎበት ቀረጥና ታክስ የሚሰበሰብበት ነው፡፡

በመሆኑም ኮንቴነር በዕቃ መያገሪነት በጊዜያዊነት ወደ ሀገር ውስጥ ሲገባ ተመልሶ ከአገር ለመውጣቱ ማረጋገጫ እስኪቀርብ ድረስ የቀረጥና ታክሱን መጠን ዋስትና እንዲያዝበት መደረጉ አስፈላጊ ነው፡፡ ኮንቴነሩ ከአገር መውጣቱን የሠነድ ማረጋገጫ በወቅቱ ሲቀርብ ዋስትናው ይወራረድበታል፡፡ ምንም እንኳን በተለያየ ጊዜ ሰርኩላር መተላለፉ የሚታወቅ ቢሆንም ወቅቱ የሚጠይቀውን አገልግሎት ካለመስጠቱም በላይ በቅ/ጽ/ቤቶች መካከልም ወጥ የሆነ አፈፃፀም ማስፈን ባለመቻሉና የመልካም አስተዳደር ችግር ሆኖ አሉታዊ ተጽእኖ እያሳደረ ይገኛል፡፡ በዚህ መሠረት ወጥነት ያለው ቀላልና ግልጽ የሆነ የአሰራር ማሻሻያ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ይህ የተሻሻለው የአሠራር ሥርዓት ተዘጋጅቷል፡፡

## 2. ዓላማ

ከውጭ አገር ጭነት ይዘው በጊዜዊነት ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ ኮንቴነሮች በተፈቀደው ጊዜ ገደብ ውስጥ ተመልሰው ከአገር መውጣታቸውን ለማረጋገጥ የመረጃ አያያዝ ሥርዓት መዘርጋትና መተማመኛ የሚሆን የቀረጥና ታክስ መጠን ዋስትና በማስያዝ እንዲፈፀም ከማስፈለጉም በላይ በአፈፃፀም ሂደት ውስጥ ሲያጋጥም የነበረውን የመልካም አስተዳደር ችግሮች መቅረፍና ለኤክስፖርት ዕቃዎቻችን በቂ መጠን ያለው ኮንቴነር እንዲቀርብ ሁኔታዎችን በማመቻቸትና ከአገር መውጣቱ ሲረጋገጥ የተያዘው ዋስትና የሚወራረድበት የአሠራር ሥርዓት መፍጠር ነው፡፡

## ለተመላሽ ኮንቴነር ስለሚያዝ ዋስትና

## 3. ለተመላሽ ኮንቴነር የሚያዙ የዋስትና ዓይነቶች

- 3.1. ጥሬ ገንዘብ
- 3.2. የባንክ ጋራንቲ
- 3.3. የመድህን ዋስትና
- 3.4. የግዴታ ደብዳቤ ናቸው፡፡

## ስለዋስትና ዓይነትና የተጠቃሚ ሁኔታ

### 4. የሚሰጠው የዋስትና ዓይነት

4.1. ማንኛውም አስመጪ ለተመላሽ ባዶ ኮንቴነር የሚያስይዘው ዋስትና የቀረጥና ታክሱን መጠን በጥሬ ገንዘብ ወይም በባንክ ጋራንቲ ወይም የመድን ዋስትና በማስያዝ ነው፡፡

4.2. የመርከብ አጓጓዥ ድርጅቶች ወይም የመርከብ ወኪሎች ለሚያስመጧቸው እና በአገር ውስጥ ከአስመጪዎች ለተረከቧቸው ባዶ ኮንቴነሮች የሚሰጡት የግዴታ ደብዳቤ በማቅረብ ሲሆን ከአስመጪዎች ባዶ ኮንቴነር ሲረከቡ መረከባቸውን በደብዳቤ ለሚመለከተው የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት በማሳወቅ ይሆናል፡፡

4.3. ኤምባሲዎች፣የቆንስላ ጽ/ቤቶች፣ዓለም አቀፍ ድርጅቶች እና የዲፕሎማቲክ መብት ያላቸው ሠራተኞችና ተቋማት ለሚያስመጡት የዕቃ መያገር ኮንቴነር የሚያዘው ዋስትና ሰራተኛ ከሆነ ከሚሰራበት ተቋም ወይም እራሱ ተቋሙ የሚያስገባ ከሆነ በሚያቀርበው ግዴታ ደብዳቤ መሠረት ይሆናል፡፡

4.4. በአምራች ላኪዎች ወይም በአምራቾች ስም ወደ አገር ውስጥ የሚገባ ኮንቴነር የሚጠየቀው ዋስትና ከአምራች ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ወይም ተወካይ በሚቀርበው ግዴታ ደብዳቤ መሠረት ይሆናል፡፡

4.5. በኮንቴነር ተርሚናል ስራ ላይ የተሰማሩ በሕግ የተፈቀደላቸው አካላት የሚቀርብ ደብዳቤ መሠረት ይሆናል፡፡

### 5. የአስመጪዎች፣የንግድ መርከብ ድርጅቶች ወይም የመርከብ ወኪሎች ግዴታ

5.1. የማንኛውም መደበኛ አስመጪና የተመላሽ ኢትዮጵያዊ ግዴታ

5.1.1. ዋስትና ተይዞበት በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ የገባው ተመላሽ ኮንቴነር በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ ከአገር ማውጣት ወይም በአገር ውስጥ ለሚገኝ የንግድ መርከብ ድርጅት ወይም የመርከብ ወኪል ለሆኑ ድርጅቶች በማስረከብ ማረጋገጫ ደብዳቤ ማቅረብ ይኖርበታል፣ወይም

5.1.2. ዋስትና ተይዞበት በጊዜያዊነት ወደ አገር የገባ ተመላሽ ባዶ ኮንቴነር የባለሥልጣኑ ቅ/ጽ/ቤት ዋስትናውን ከተቀበለበት ቀን ጀምሮ በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ የወጪ ዕቃ ጭኖ ለሚልክ ላኪ ድርጅት ያስረከበ እንደሆነ ያስመጣው ኮንቴነር ቁጥርና የወጪ ዲክላራሲዮን ቁጥር በመጥቀስ ለሚመለከተው የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት በማቅረብ በሲስተም ቫሊዴት መደረጉን እንዲረጋገጥለትና ግዴታው እንዲነሳለት ማቅረብ ይቻላል፡፡ ወይም

5.1.3. ዋስትና ተይዞበት በጊዜያዊነት ወደ አገር የገባው ተመላሽ ባዶ ኮንቴነር የባለሥልጣኑ ቅ/ጽ/ቤት ዋስትናውን ከተቀበለበት ቀን ጀምሮ በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ አስጭኖ ከአገር ለማስወጣት በኮንቴነር መመለሻ ቅጽ ላይ የአስመጪው ስም ወይም ድርጅት ስም፣የኮንቴነር ቁጥሩን፣የገቢ ዲክላራሲዮን ሴሪ ቁጥር፣የማጓጓዣ ሠሌዳ ቁጥርና የሾፌር ስም በመጥቀስ ዋስትና ላስያዘበት የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት የትራንዚት ቡድን በማቅረብ መውጫ መጠየቅ አለበት፡፡

5.1.4. ከላይ በተራ ቁጥር 5.1.3 መሠረት ኮንቴነሩ ከአገር ለመውጣቱ የተረጋገጠበት የኮንቴነር መመለሻ ቅጽ ከሾፌር በመረከብ ለመዳረሻ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት የትራንዚት ቡድን በማቅረብ ያስያዘውን የዋስትና ግዴታ እንዲነሳለት ማቅረብ፣ወይም

5.1.5. ዋስትና ተይዞበት በጊዜያዊነት ወደ አገር የገባው ተመላሽ ባዶ ኮንቴነር ዋስትናው ተቀባይነት ካገኘበት ቀን ጀምሮ በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ ተመልሶ ከአገር የወጣውን ባዶ ኮንቴነር የወደብ አስተዳደሩ ለመረከቡ ኦርጅናል ኢንተርቼንጅ ወይም ኮፒ ኢንተርቼንጅ ላይ በማህተም የተረጋገጠ ማስረጃ ማቅረብ ወይም ኮንቴነሩ መርከብ ላይ መጫኑን የሚገልጽ የማስጫኛ ሰነድ ማቅረብ አለባቸው፡፡

5.2. የንግድ መርከብ ድርጅቶች ወይም የመርከብ ወኪሎች ግዴታ

5.2.1. የንግድ መርከብ ድርጅት፣የውጭ መርከብ ውክልና ያላቸው ድርጅቶች ከውጭ ወደ አገር ውስጥ ከጭነት ጋር ላስመጧቸው ወይም ከአስመጪዎች ለተረከቧቸው ባዶ ኮንቴነሮች በአጥር የተከለለ የማከማቻ ቦታ መኖር አለበት፡፡

5.2.2. የውጭ መርከብ ውክልና ያላቸው ድርጅቶች በማንኛውም አስመጪ ዋስትና ተይዞበት በጊዜያዊነት ወደ አገር የገባውን ተመላሽ ባዶ ኮንቴነር መረከባቸውን የሚያረጋግጥ ደብዳቤ ዋስትና ለተያዘበት የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት መላክ /ማሳወቅ/ አለበት፡፡

5.2.3. ዋስትና ተይዞበት በጊዜያዊነት ወደ አገር የገባው ተመላሽ ባዶ ኮንቴነር የባለሥልጣኑ ቅ/ጽ/ቤት ዋስትናውን ከተቀበለበት ቀን ጀምሮ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ አስጭኖ ከአገር ለማስወጣት በኮንቴነር መመለሻ ቅጽ ላይ የአስመጪው ስም ወይም ድርጅት ስም፣የኮንቴነር ቁጥሩን፣የገቢ ዲክላራሲዮን ሴሪ ቁጥር፣የማጓጓዣ ሰሌዳ ቁጥርና የሾፌር ስም በመጥቀስ ዋስትና ላስያዘበት የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት የትራንዚት ቡድን በማቅረብ መውጫ መጠየቅ አለበት፡፡

5.2.4. ከላይ በተራ ቁጥር 5.2.3 መሠረት ኮንቴነሩ ከአገር ለመውጣቱ የተረጋገጠበት ቅጽ ከሾፌር በመረከብ ለመዳረሻ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት የትራንዚት ቡድን በማቅረብ ያስያዘውን የዋስትና ግዴታ እንዲነሳለት ማድረግ፣ወይም

5.2.5. የንግድ መርከብ ድርጅት፣የውጭ መርከብ ውክልና ያላቸው ድርጅቶች ከውጭ ወደ አገር ውስጥ ከጭነት ጋር ላስመጧቸው ወይም ከአስመጪዎች ለተረከቧቸውና ለጉምሩክ መረከባቸውን በደብዳቤ ላረጋገጧቸው ተመላሽ ኮንቴነሮች የባለሥልጣኑ ቅ/ጽ/ቤት ዋስትናውን ከተቀበለበት ቀን ጀምሮ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ መልሰው ከአገር ማስወጣታቸውን የሚያረጋግጥ Shipped on board የሚል የማስጫኛ ሰነድ ማቅረብ፣ ወይም

5.2.6. የንግድ መርከብ ድርጅትና የውጭ መርከብ ድርጅት ወኪል የሆነ ተመላሽ ኮንቴነሩን ለላኪ በሚያስረክብበት ወቅት የላኪው ስም፣የኮንቴነር ቁጥር፣የላኪው ቲን ቁጥር እና የወጪ ዲክላራሲዮን ሴሪ ቁጥር በመጥቀስ የተሟላ መረጃ ዋስትና ላስያዘበት የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት የትራንዚት ቡድን በየወሩ እንቅስቃሴውን የሚያሳይ ሪፖርት ማቅረብ፣ወይም

5.2.7. ዋስትና ተይዞበት በጊዜያዊነት ወደ አገር የገባው ተመላሽ ባዶ ኮንቴነር የባለሥልጣኑ ቅ/ጽ/ቤት ዋስትናውን ከተቀበለበት ቀን ጀምሮ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ተመልሶ ከአገር መውጣቱን የወደብ አስተዳደሩ ለመረከቡ በኦርጅናል ኢንተርቼንጅ ወይም በኮፒ ኢንተርቼንጅ ማህተም የተረጋገጠ ማስረጃ ሲቀርብ የገቡትን ግዴታ እንዲነሳለት ማድረግ ይችላል፡፡

## ተመላሽ ኮንቴነር የማረጋገጥና ዋስትና የማወራረድ ግዴታ

6. ተመላሽ ኮንቴነር የማረጋገጥ ግዴታ

6.1. የመውጫ በር የጉምሩክ ጣቢያ ተግባርና ኃላፊነት

6.1.1. የመውጫ በር የጉምሩክ ጣቢያ ከአገር የሚወጡ ተመላሽ ኮንቴነሮች በተመለከተ ሾፌሩ ይዞት በሚመጣ የኮንቴነር መመለሻ ቅጽ ላይ ፊርማና ማህተም በማድረግ ያረጋግጣል፣

6.1.2. የመውጫ በር የጉምሩክ ጣቢያ ከዚህ ሰርኩላር ጋር ተያይዞ በተላከው ቅጽ ላይ በመሙላት በሳምንት አንድ ጊዜ በፋክስ ወይም በኢሜል ወይም በደብዳቤ በማረጋገጥ ለመነሻ የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት የትራንዚት ቡድን ማስተላለፉ እንደተጠበቀ ሆኖ ከመነሻ የጉምሩክ ጣቢያ ተጨማሪ ማብራሪያ /ጥያቄ/ ሲቀርብ ምላሽ መስጠት አለበት፣

6.2. የመነሻ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች ተግባርና ኃላፊነት

6.2.1. የወጪ ዕቃ ተጭኖበት የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት መፈፀሙን የዚሁ ሰርኩላር ተራ ቁጥር 5፣5.1.2 እና 5.2.6 መሠረት ከአገር መውጣቱን በሲስተም ቫሊዴት መደረጉን በማረጋገጥ ለገቢ አሰባሰብና ዋስትና ሂሳቦች ክፍል በማሳወቅ ያስያዘውን የዋስትና ግዴታ እንዲነሳለት ማድረግ፣ ወይም

6.2.2. አስመጪው ወይም የመርከብ ድርጅት ወይም የመርከብ ወኪል በጊዜ ገደቡ መሠረት ባዶ ኮንቴነር ከአገር ማስወጣቱን ከመውጫው የጉምሩክ ጣቢያ በፋክስ ወይም በኢሜል ወይም በደብዳቤ ሲያቀርብለት ያስያዘውን የዋስትና ግዴታ እንዲነሳለት ማድረግ፣ወይም

6.2.3. ኮንቴነሩ መውጣቱን በጉምሩክ መውጫ በር በኮንቴነር መመለሻ ቅጽ ተረጋግጦ ሲቀርብ ግዴታው እንዲነሳለት ማድረግ፣ወይም

6.2.4. በጊዜያዊነት ዋስትና ተይዞበት ወይም በግዴታ ደብዳቤ ወደ አገር ውስጥ ገብቶ ተመልሶ ከአገር የሚወጣ ባዶ ኮንቴነር ከመውጫ በር፣ከንግድ መርከብና የውጭ መርከብ ውክልና ካላቸው ድርጅቶች የሚደርሰውን መረጃ በኮምፒዩተር አደራጅቶ መያዝ አለበት፣

6.2.5. የትራንዚት ቡድን፣የገቢ አሰባሰብና ዋስትና ሂሳቦችና የመውጫ የጉምሩክ በር ስለተመላሽ ባዶ ኮንቴነር መረጃ አያያዝና ቅብብሎሽ በተቀናጀና በተጠናከረ መልኩ መለዋወጥና መናበብ አለባቸው።

7. ዋስትና የማወራረድ ግዴታ

7.1. ማንኛውም አስመጪ ወይም የንግድ መርከብ ድርጅት ወይም የመርከብ ወኪል ማሟላት ያለበትን ግዴታ መሠረት አሟልቶ ከቀረበ ወይም ከመውጫ የጉምሩክ ጣቢያ መረጃው/ማስረጃው በደረሰ በአንድ ሣምንት ጊዜ ገደብ ያስያዘው ዋስትና ሊወራረድለት ይገባል፣

7.2. ግዴታቸውን የማይወጡትና ኮንቴነር ተመልሶ ለመውጣቱ መረጃ/ማስረጃ በጊዜ ገደቡ ውስጥ ማቅረብ ያልቻለ ማንኛውም አስመጪ ወይም ድርጅት እንደ ባለዕዳ ተቆጥሮ ያስያዘው ዋስትና ገቢ ይደረጋል፣

7.3. ማንኛውም አስመጪ ባዶ ኮንቴነር በጊዜ ገደቡ ውስጥ ወደ ውጭ ልኮ ወይም የውጭ መርከብ ውክልና ላለው ወይም ለላኪ አስረክቦ እያለ በወቅቱ ማስረጃ ሳይቀርብ ቀርቶ ያስያዘው ጥሬ ገንዘብ ወደ መንግስት ግምጃ ቤት ፈሰስ የተደረገ እንደሆነ በግዜ ገደቡ መሠረት ኮንቴነሩ ከሀገር ከወጣበት ቀን ጀምሮ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ጥያቄ ካቀረበ ተመላሽ ይደረግለታል።

8. ማስታወሻ

ከላይ በተቀመጡት የአሰራር ሥርዓት አፈፃፀም ላይ የሚከሰቱ ችግሮች ሲያጋጥሙ በወቅቱ አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ እንዲቻል ለጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ፕሮግራም ልማት ዳይሬክቶሬት ማሳወቅ ግዴታ ይሆናል።

ቅጽ-0

ቀን.............................

ቁጥር.........................

# በጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች ተመላሽ ኮንቴነር ከሀገር ተመልሶ መውጣቱን ማረጋገጫ ቅጽ

ለ ................................................ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

ከ................................................ ገቢዎችና ጉምሩክ መውጫ በር

| ተ.ቁ | የኮንቴነር ቁጥር | ወደ ሀገር ሲገቡ የተመዘገቡበት የዲ/ዮን | | ኮንቴነሩ ከሀገር የወጣበት ቀን | ኮንቴነሩ ከሀገር ሲወጣ የወጪ ዕቃ | | ዕቃ የያዘ ከሆነ የወጪ ዲ/ዮን | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ቁጥር | ቀን | | የያዘ | ባዶ | ቁጥር | ቀን |
| | | | | | | | | |
| | | | | | | | | |
| | | | | | | | | |
| | | | | | | | | |
| | | | | | | | | |
| | | | | | | | | |
| | | | | | | | | |
| | | | | | | | | |
| | | | | | | | | |
| | | | | | | | | |
| | | | | | | | | |
| | | | | | | | | |

ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት ኮንቴነሮች ከሀገር መውጣታቸውን እናረጋግጣለን።

**ቅፁን ያዘጋጀው ሠራተኛ**

ስም ..................................

ፊርማ..............................

ቀን ..................................

**ቅፁን ያፀደቀው ኃላፊ**

ስም ..................................

ፊርማ ..............................

ቀን ..................................

ቅጽ-02

ቀን.........................

ቁጥር.........................

## በጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች ከሀገር ተመልሰው ለሚወጡ ኮንቴነሮች መመለሻ ቅጽ

ለ ............................................ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

ከ............................................ ድርጅት

| ተ.ቁ | የአስመጪው ስም/ድርጅት | የኮንቴነር ቁጥር | ኮንቴነሩ ዕቃ ጭኖ ሲገባ የተመዘገበበት ዲክላራሲዮን | | ኮንቴነሩን ጭኖ የሚወጣው ሾፌር/ትራንስፖርት ድርጅት ስም |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ቀን | ቁጥር | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |

ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት ኮንቴነሮች ከሀገር እንዲወጣ እጠይቃለሁ።

**የጠያቂው**

ስም ..............................

ፊርማ..............................

ቀን ..............................

**ጥያቄውን ተቀብሎ ያፀደቀው የጉምሩክ ኦፊሰር**

ስም ..............................

ፊርማ ..............................

ቀን ..............................